# ኮቪድ-19 በቤት ውስጥ ምርመራዎች የእርስዎን የምርመራ
## ውጤት መረዳት

April 15, 2022 9:49 AM AMHARIC

## አውንታዊ ውጤት ቢኖረኝስ?

ቫይረሱ በሰውነትዎ ውስጥ ያለ ሲሆን ምንም ዓይነት የሕመም ምልክት ባይኖርብዎም እንኳ ለሌሎች ሊያሰራጩ ይችላሉ። ተከትብዎ ይሁን አይሁን እንዲህ ማድረግ አለብዎት፦

1. የህክምና ክትትል ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር እቤት ይቆዩ። ቢያንስ ለ 5 ቀናት ራስዎን ከሌሎች ቤት ውስጥ ካሉ ቤተሰቦች ያግልሉ። ከ 5 ቀን በኋላ፣ ከቤት መውጣት ይችላሉ እንዲህ ከሆኑ፦
    - ትኩሳትን የሚቀንሱ መድሃኒቶች ሳይኖሩ ቢያንስ ለ24 ሰዓታት ትኩሳት ያልነበረባቸው እና እየተሻሻሉ ያሉ ቀላል ምልክቶች ብቻ ያላቸው ሲሆን፣ እና
    - ለ 5 ተጨማሪ ቀናት በሌሎች ዙሪያ በጥንቃቄ ጭንብል አድረገው መቀጠል የሚችሉ። ጭምብል ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ለ 5 ተጨማሪ ቀናት ማግለልዎን ቀጥሉ።
    - ይህ መመሪያ ለአብዛኞቹ ሰዎች ይሠራል። እንደ ጤና እንክብካቤ ባሉ ከፍተኛ-ስጋት ያለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ ረዘም ላለ ጊዜ ብቻዎን ማግለል ሊያስፈልግዎ ይችላል። አሠሪዎን ይጠይቁ።



2. በተቻለ ፍጥነት ለጤና አገልግሎት ሰጪዎ ይደውሉ። እንደ እድሜዎ እና/ወይም እንደ ጤና ሁኔታዎ ህክምና ሊኖር ይችላል። አንዳንድ የ ኮቪድ-19 ህክምናዎች ምልክቶች ከታዩ በ 5 ቀናት ውስጥ መጀመር አለባቸው። የጤና አገልግሎት ሰጪ ከሌለዎት፣ አንድን እርዳታ ለማግኘት 211 ይደውሉ።
3. ለቅርብ እውቂያዎችዎ እና ለቤተሰብ አባላት የምርመራ ውጤትዎ አዎንታዊ እንደሆነ ይንገሯቸው። የጊዜ ጉዳይ ወሳኝ ነው! እንደ በሌሎች ዙሪያ ጭምብል መልበስ እና መመርመር የመሰሉትን በማድረግ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ። በሀገራቸው የህዝብ ጤና ድርጣቢያ ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ወይም 211 መደወል ይችላሉ።.
    - ምልክቶች ኖሮብዎት ቢያውቅም ወይም ቢኖርብዎም፦ የሕመም ምልክቶችዎ ከመጀመራቸው ከ 2 ቀናት በፊት በቅርብ የቅርብ ግንኙነት የነበርዎትን ሰዎች ያነጋግሯቸው።
    - ምልክት ከሌለዎት ወይም ካልነበርዎት፦ ኮቪድ-19 ምርመራዎን ከመውሰድዎ 2 ቀናት በፊት ከመጀመሪያ ጋር የቅርብ ግንኙነት ከነበርዎ ሰዎች ጋር ይነጋገሩ።

## አዎንታዊ የሆነ የምርመራ ውጤት ሪፖርት ማድረግ የምችልበት መንገድ ምንድን ነው?

ሥራዎ ከሕዝብ ጋር ግንኙነት ማድረግን የሚያካትት ከሆነ የኮቪድ-19ን ስርጭት በመገደብ ለማገዝ እንዲችሉ ለአሠሪዎ መንገር ይኖርብዎታል። አለበለዚያ በቤት ውስጥ የተደረገን አውንታዊ ምርመራ ለማንም ማሳወቅ አያስፈልግዎትም።

ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ድጋፍ ካስፈለገዎት እና አዎንታዊ የምርመራ ውጤትዎን በተመለከተ ከህዝብ ጤና ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ፣ በ 503-988-3406 ወይም diseasereport@multco.us ላይ Multnomah County Public Health መደወል ወይም ኢሜይል መላክ ይችላሉ። ለአሠሪዎ ወይም የቅርብ እውቂያዎችዎን፣ ቤት ለመቆየት የሚያስችል መርጃዎች ለማግኘት እንዲሁም ሊኖርዎት የሚችሉ ሌሎች ጥያቄዎች በመመለስ ሊረዱዎት ይችላሉ።

ተጨማሪ የጤና መረጃ ወይም በኦሪገን የጤና ባለስልጣን ፖዚቲቭ ኮቪድ ምርመራ ድርጣቢያ https://govstatus.egov.com/or-oha-covid-19-positive-test ላይ ራስን በመለየት እና ተገልሎ በመኖር እገዛ ያግኙ ወይም የጉዳዮቻቸውን ድጋፍ ሆትላይን በ 866-917-8881 ይደውሉ።

## ኣሉታዊ ውጤት ቢኖረኝስ?

ከታመሙ የሕመም ምልክቶችዎ እስኪሻሻሉ ድረስ ከቤትም ሆነ ከሌሎች ርቀው መቆየት ይኖርብዎታል፣ ምንም እንኳ ምርመራዎ አሉታዊ ቢሆንም።

ከ ኮቪድ-19 ያለበት ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ከነበረዎት፣ ለቫይረሱ ተጋልጠው ነበር እና ሌሎችም እንዲታመሙ ሊያድርጉ ይችላሉ። ለከፍተኛ ስጋት በሚያጋልጡ ሁኔታዎች ውስጥ ካልኖሩ ወይም ካልሠሩ በስተቀር እንደ ጤና ጥበቃ ወይም አንዳንድ የቡድን መኖሪያ ቤቶች ተገልለው መኖር አያስፈልግዎም።

- ለመጨረሻ ጊዜ ከተጋለጡበት ጊዜ አንስቶ ለ10 ቀናት ራስዎን ይከታተሉ። የት እና ከማን ጋር እንደሚሆኑ ያስቡ። ለከባድ ኮቪድ-19 ከፍተኛ ስጋት የተጋለጡ ሰዎችን ከሰው ጋር ያለዎትን ግንኙነት በመገደብ ወይም ለእነዚያ 10 ቀናት በዙሪያቸው ጭምብል በመልበስ መጠበቅዎን መቀጠል ይችላሉ።
- የቤት ውስጥ ምርመራ ከወሰዱ በመደበኛ የጤና አገልግሎት ሰጪዎ በኩል ሌላ ኮቪድ-19 ምርመራ ለማግኘት መሞከር ወይም ከ 1-2 ቀን በኋላ ሌላ የቤት ውስጥ ምርመራ መውሰድ ይችላሉ።

**የ ኮቪድ-19 ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡-**

- ትኩሳት ወይም ብርድ-ብርድ ማለት
- ሳል
- የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር
- ድካም
- የጡንቻ ወይም የሰውነት ሕመም
- ራስ ምታት
- አዲስ የመቅመስ ወይም የማሽተት ችግር
- የጉሮሮ ህመም
- የአፍንጫ መታፈን ወይም የንፍጥ መኖር
- ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ
- ተቅማጥ

**እነዚህ ከባድ ምልክቶች ካሉብዎት 911 ይደውሉ፡-**

- የመተንፈስ ችግር
- በደረት ወይም በሆድ ውስጥ ያለው ሕመም ወይም ግፊት
- ፈሳሽ ነገር መጠጣት አለመቻል ወይም ከጠጡ በኋላ ማስመለስ
- ያልነበረ ግራ መጋባት ወይም መንቃት አለመቻል
- ግራጫማ ወይም ሰማያዊ ከንፈር ወይም ፊት

